# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 328 ነሃሴ 16 2006 ገጽ


ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በወያኔ አገዛዝ ሥር ባለችው ኢትዮጵያ ውስጥ ምስጢራዊና ማዕከላዊነትን ያልጠበቁ ትናንሽ ስብስቦች ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ ብሎ ያምናል። ስለሆነም ግንቦት 7፣ እያንዳንዱ ለሀገሩ፣ ለነፃነቱ፣ ለክብሩ፣ ለፍትህ ግድ ያለው ወጣት ከሚመስሉትና ከሚያምናቸው ጥቂት ወዳጆቹ ጋር በምስጢር እንዲደራጅ አጥብቆ ይመክራል። የተደራጁ ስብስቦች ግንቦት 7ን ማግኘት ወይም ግንቦት 7 እነዚህን ስብስቦች ማግኘት አስቸጋሪ አይሆንም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ለማግባባት ያደረገው ጥረት ከሸፈ

በአዲስ አበባ ጊዮን ሆቴል በዝግ በተካሄደው የፋሽስቱ ወያኔ የአምባሳደሮችና የቆንስላ ጀኔራሎች አመታዊ ግምገማና ውይይት ላይ የጉጅሌው ወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተብየ ቴዎድሮስ አድሃኖ በውጭ አገራት ከሚኖሩ የዲያስፖራ ማህበረሰብ አባላት ጋር ለመቀራረብና ለመግባባት የተደገው ጥረት ሙሉ በሙሉ አልተሳካም ሲል ለጉጅሌው ሹማምንቶች መግለፁን የውስጥ ምንጮችን አመልክቷል። የፋሽስቱ ወያኔ ተላላኪ ቴዎድሮስ አድሃኖ በመላው አለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገዛዙና በሹማምንቱ ላይ እያደረሱባቸው የሚገኘውን ተቃውሞ ለማሳያነት በማንሳት በተለይም ባለፉት ሳምንታት በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ፣ ሎሳንጀለስ፣ ዳላስና ሌሎችም ግዛቶች ላይ ኢትዮጵያውያን በነቂስ በመውጣት በፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንት ላይ ያካሄዱዋቸው ቁጣን የቀላቀሉ ተከታታይ የተቃውሞ ሰልፎች አገዛዙ በዲያስፖራው ማህበረሰብ ለመተፋቱ ማሳያ እንደሆኑ በመግለጽ ተቃውሞው በዚህ ከቀጠለ በአገዛዙ ላይ ከፍተኛ ውድቀት እንደሚያስከትል በመግለጽ ሹማምንቱ በተመደቡበት አገራት ዲያስፖራውን ለመሸንገል ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉ መታዘዛቸውን የውስጥ ምንጮችን አመልክቷል። በዝግ በተካሄደው የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንቶች ግምገማ ላይ በተለይ በአሜሪካ ጉብኝት ወቅት በኢትዮጵያውያን የተደረጉ ቁጣ የተቀላቀለባቸው የተቃውሞ ሰልፎች እና የአገዛዙ ሹማምንትን በማሳደድ የተደረጉ የማዋረድና የማሸማቀቅ እንቅስቃሴዎች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት ውይይት እንደተደረገባቸው ለማወቅ ተችሏል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የቦሌ መንገዶች በድምጻችን ይሰማ የተቃውሞ ጽሁፎች አሸብርቀዉ ዋሉ

የፋሽስቱ ወያኔ ተላላኪ ቴዎድሮስ አድሃኖ በእስር ላይ የሚገኙትን የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴዎችን በተመለከተ ጓንታናሞ ከታሰሩ አሸባሪ እስረኞች ጋር ግንኙነት እንዳላቸው አረጋግጠናል የሚል መሰረተ ቢስ ውንጀላ መሰንዘሩን ተከትሎ በህዝበ ሙስሊሙና በአስተባባሪው ድምፃችን ይሰማ ዘንድ ዳግም ቁጣ ማገርሸቱን ለማወቅ ተችሏል። ካለፉት 3 አመታት ጀምሮ ድምፃችን ይሰማ ህዝበ ሙስሊሙን በማስተባበር የአገዛዙን የእምነት ጣልቃ ገብነትና አገዛዙ በሰላማዊው ህዝበ ሙስሊም ላይ እያደረሰ የሚገኘውን ግድያ፣ ጭቆናና አፈና ላይ ተቃውሞውን በተለያየ መንገድ እየገለጸ ሲሆን አሁንም የፋሽስቱን ቱልቱላ ቴዎድሮስ አድሃኖን መሰረተ ቢስ ውንጀላ ተከትሎ ተቃውሞውን በተጠናከረ ሁኔታ ለማካሄድ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ድምፃችን ይሰማ በአዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ የየተቃውሞ ጽሁፎችን እንደበተነ ዘጋቢያች ከስፍራው የላከልን መረጃ ያመለክታል። በተለያዩ አካባቢዎች ፋሽስቱ ወያኔ በሐይማኖት ጣልቃ ገብነቱን ያቁም፣ ኮሚቴዎቻችን ይፈቱ፣ የሚሉ የተቃውሞ ፅሁፎች እየተፃፉ ሲበተኑ የቆዩ ሲሆን ቅዳሜ እለት በቦሌም በተመሳሳይ መልኩ የተቃውሞ ጽሁፎች በግድግዳና በየመንገዶች ላይ ጭምር ተጽፈው ማደራቸውን ለማወቅ ተችሏል:: ከወሎ ሰፈር እስከ ቦሌ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እየሰጠ ያለው ስልጠና ከፍተኛ ተቃዉሞ ገጠመዉ

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ለዩንቨርስቲ ተማሪዎች ለተከታታይ 15 ቀናት በአገዛዙ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች ዙርያ አስገዳጅ ሥልጠና እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን በተለያዩ የማሰልጠኛ ተቋማት ላይ በሰልጣኝ ተማሪዎች የሚሰነዘሩት በርካታ ጠንካር ያሉ ጥያቄዎችና ትችቶች የፋሽስቱን ቱባ አመራሮች እና ካድሬዎች ድንጋጤ ውስጥ ከቷቸው እንደሚገኝ ዘጋቢዎቻችን ከየተቋማቱ የላኩልን መረጃ ያመለክታል። ተማሪዎቹ በየፊናቸው የሚያነሷቸው ወቅታዊ አገራዊ ጥያቄዎችና ትችቶች በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ትችቶቹና ጥያቄዎቹ በጉጅሌዎቹ ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ መፍጠራቸውን ያደረሱን ዘጋቢዎቻችን የፋሽስቱ ቅጥረኞች ለሚሰነዘሩት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት አለመቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የመከላከያ ሰራዊት አባላት የዘረኞች መሳሪያ አንሆንም እያሉ በመኮብለል ላይ መሆናቸው ተሰማ

በሁሉም የመከላከያ እዞች ከዕለት ዕለት እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሰራዊት አባላት በመክዳት በመጥፋት ላይ መሆናቸውን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ይህንን ተከትሎ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በመላ አገሪቱ የሚኖሩ የቀድሞ የመከላከያ ሰራዊት አባላትን በመሸንገል ዳግም ለመቅጠር ጥሪ ማቅረቡን ለማወቅ ተችሏል። በየወረዳዎች የተለጠፉት ማስታወቂያዎች እንደሚያመለክቱት በተለያዩ ጊዜያት በአገር መከላከያ ሰራዊት ሲያገለግሉ የነበሩና በተለያዩ ጊዜያት ወደ ወረዳቸው የተመለሱ የሰራዊት አባላትን በሙሉ እስከ ነሃሴ 21 እየቀረቡ እንዲመዘገቡ ያዛል። ማስታወቂያዎቹ የወጡት መከላከያን እየከዱ የሚጠፉ የሰራዊት አባላት ቁጥራቸው ከዕለት ዕለት በመበራከቱና በተደጋጋሚ አዳዲስ ተመልማዮችም ለመቅጠር በወጡት ማስታወቂያዎች ተመዝጋቢ በመጥፋቱ ነባሮችን በመመለስ ስራ ለመስራት መሆኑን አይቀርም ሲል ዘጋቢያችን የውስጥምንጮችን አመልክቷል።

የአገዛዙ ዘረኝነት፤ አምባገነናዊነት፤ በሰራዊቱ አባላት በተደጋጋሚ የሚቀርበው የጥቅማ ጥቅም ጥያቄ በአገዛዙ ተቀባይነት ባለማግኘቱ በሰራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ ቅራኔን በመፍጠሩ ለሰራዊቱ መክዳት ከብዙ በጥቂቱ ምክንያቶች መሆናቸውን መዘገባችን ይታወሳል። በእያንዳንዱ እዝ በመሪነትና በተቆጣጣሪነት የተመደቡ የአገዛዙ ቅጥረኞች ሳይቀር በተስፋ መቁረጥ ሞራላቸው በመውደቁ የሰራዊት አባላትን መቆጣጠር ባለመቻላቸው የሰራዊቱን መክዳት አባብሶታል ይገኛል።

## የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የአገራችን ችግሮች በስልጠና አይፈቱም አሉ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ "የመንግስትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ለከፍተኛ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማስተዋወቅ" በሚል ሽፋን በአገሪቱ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ዉስጥ የጀመረው ስልጠና "ችግሮች በስልጠና አይፈቱም "የሚል መፈክር ባነገቡ ተማሪዎች ከየአቅጣጨዉ ከፍተኛ ተቃዉሞ እየገጠመዉ መሆኑ ተሰማ። ተማሪዉን ያለፈቃዱ ከአገዛዙ ጎን ለማሰለፍ በሚደረገዉ በዚህ ስልጠና ላይ ከእሱ ባላይ እዉቀት ያለዉን የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ለማሰልጠን የመጡት መሀይም የወያኔ ካድሬዎች ተማሪዎች በተከታታይ የሚያነሷቸዉን ጥያቄዎች መመለስ አቅቷቸዉ ሲበሳጩና ተማሪዉን ሲገላምጡ ታይተዋል።

በወሎ ዩኒቨርስቲ በመካሄድ ላይ ባለው ስልጠና ተማሪዎች ኢህአዴግ እራሱን ከቀድሞ ስርአቶች ጋር ማወዳደሩን አቁሞ ስርዐቱ እሱ እራሱ ከሰራቸዉ ስራዎች ጋር እንዲመዘን ጠይቀዋል። የቀድሞ ስርአቶች ያልተማሩ በመሆናቸው ስህተት ቢሰሩ አይገርምም ያሉት ተማሪዎች፣ የእነሱን ስህተት ብቻ እያጎላችሁ የራሳችሁን ድክመት ለመሸፈን ትሞክራላችሁ ሲሉ ወቅሰዋል። የብሄርን ጉዳይ አስመልክቶ ደግሞ እውነት ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ብሄር ብቻ ነው ያለው እንዴ ሲሉ ጠይቀዋል። ህወሃት በአገሪቱ ያሉ ቁልፍ ቦታዎችን መቆጣጠሩን የተቹት ተማሪዎች፣ ህወሃት በአጼ ሚኒሊክ ዘመን የተፈጸሙትን ድረጊቶች እያነሳ አማራና ኦሮሞን ለማጋጨት እየሰራ ነው ሲሉ ነቅፈዋል።

ከሙስሊሙና ከክርስቲያን ተማሪዎች ከፍተኛ ጥያቄ ያስነሳው የሃይማኖት ጉዳይ ሲሆን፣ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ እጁን ማስገባቱን፣ የሙስሊም የመፍትሄ አፈላላጊኮሚቴ አባላት ያለአገባብ መታሰራቸውን ተማሪዎች አንስተዋል።አገር በዶክመንታሪ አይመራም የሚሉት ተማሪዎች፣ የሃይማኖት እና የፖለቲካ መሪዎችን ማሰሩ በህዝብ ዘንድ እንዲጠላ ከማድረጉም በተጨማሪ ዋጋ ያስከፍለዋል ሲሉ ተማሪዎች ተናግረዋል።

ኢህአዴግ ልማት አላማጣም በማለት የተናገሩ አንዳንድ ተማሪዎች፣ መጣ የተባለውም ልማት ግሎባላይዜሽን ያመጣው እንጅ በጎንደር ዩኒቨርስቲ በመካሄድ ላይ ባለው ውይይት ደግሞ ተማሪዎች የህዝባዊ ወያን ሃርነት ትግራይ ንብረት ስለሆነው ኢፈርት ኩባንያ ባለቤትነት ጥያቄ አንስተዋል። የመንግስት ድርጅቶች ወደ ግል እየዞሩ ቢሆንም፣ በእጅ አዙር የሚዟዙት የእናት ባለስልጣናት ናቸው በማለት የተናገሩት ተማሪዎች፣ በቅርቡ በታሰሩት በአነ አቶ መላኩ ፋንታ ዙሪያ የህወሃቱ ኢፈርት እጅ አለበት በማለት አስተያየት ሰጥተዋል። ኢፈርት የአገሪቱን አብዛኛውን ሃብት ጠቅልሎ መያዙን፣ ከታክስ ነጻ በሚያስገባቸው እቃዎች ዙሪያ ተቃውሞ አቀረቡት አቶ መላኩ ፋንታ ተለይተው እንዲታሰሩ መደረጉን ተማሪዎች ተናግረዋል። ኢፈርትን በተመለከተ ለተነሳው ጥያቄ አወያዮች መልስ ሳይሰጡ አልፈውታል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ከወያኔ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ስልጠናዎች የተረዳነው: - ወጣቱ ለለውጥ ዝግጁ ነው፤ የቀረው ድርጅት ነው

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተመሠረቱበት ዓላማ የእውቀትና ጥበብ መበልፀጊያና ማስፋፊያ እና የምርምር ማዕከላት እንዲሆኑ ነው። እውቀትና ጥበብ እንዲበለፅጉ እና የምርምር ሥራዎች እንዲዳብሩ የአካዳሚ ነፃነት መኖሩ ቁልፍ ጉዳይ ነው። የአካዳሚ ነፃነት ሳይኖር መምህራኑም ተማሪዎቹም በነፃነት ማሰብ፣ አስቸጋሪ ጥያቄዎችን ማንሳት እና ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለመሻት መመራመር አይችሉም። የአካዳሚ ነፃነት ሳይኖር የተለያዩ እይታዎችንና ንድፈሀሳቦችን በገለልተኛነትና በሀቀኝነት መመርመር አይቻልም። በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የአካዳሚ ነፃነት እንዲኖር ተቋማቱ ከፓርቲ ፓለቲካ ገለልተኛ መሆን ይኖርባቸዋል። አንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የአንድ ፓርቲ ርዕዮተ ዓለም አራማጅ ከሆነ ተቋሙ የፓርቲው ካድሬዎች ማሰልጠኛ ሆነ ማለት ነው። ዛሬ በአገራችን የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙበት ሁኔታ ይህ ነው። የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወያኔ ካድሬዎች ማሰልጠኛ ሆነዋል። ይህ አጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወደ ህወሓት ካድሬ ማሰልጠኛነት መዝቀጥ አንድ ተጨባጭ ማስረጃ ሰሞኑን ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በፕላዝማ ቴሌቪዥን አማካይነት በመሰጠት ላይ ያለው ፕሮፖጋንዳ ነው። በዚህ ፕሮፖጋንዳ ያልተጠመቀ ተማሪ የሚቀጥለው ዓመት መደበኛ ትምህርት አይቀጥልም በማለት ተቋማቱ ለካድሬ ማሰልጠኛነታቸው እውቅና ሰጥተዋል።

በዚህ ብዙ የአገር ሀብትና ጊዜ በፈሰሰበት ቅስቀሳ፣ የወያኔ ካድሬዎች ዘረኛና ከፋፋይ ፓሊሲዎቻቸውን ማር ቀብተው ወጣቱን ለመጋት እየጣሩ ነው። ለፓርቲ ቅስቀሳ የመንግሥትን መዋቅር መጠቀም በራሱ ወንጀል ቢሆንም ከዚህ በላይ ጉዳት ያለው ደግሞ የፕሮፖጋንዳው ይዘትና ዓላማ ነው። ወያኔ/ኢሕአዴግ ሁሉንም ነገር የሚያውቅ፤ ሁሉንም ነገር ማድረግ የሚችል ተደርጎ የተዘጋጀው ፕሮፖጋንዳ በትውልድ ላይ የሚያስከትለው የእውቀትና የሥነ ልቦና ኪሳራ ከፍተኛ ነው።

በዚህ “ስልጠና” ተብሎ በሚሞካሸው ርካሽ ፕሮፖጋንዳ አማካይነት አድርባይ የሆነው ወያኔ ወጣቱን ለአድርባይነት እያዘጋጀው ነው። የወያኔ ዓላማ የኢትዮጵያ ወጣት መስሎና ዋሽቶ አዳሪ እንዲሆን ማድረግ ነው። የስልጠናው ዓላማ ወጣቶች ለግል ሕወታቸው ምቾች ሲሉ የወያኔ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሆኑ ማድረግ ነው። የስልጠናው ዓላማ **“ወይን ለኑሮ”** ተቀባይነት ያለው የኑሮ ዘይቤ ለማድረግ ነው። ይህ ደግሞ የከፍተኛ ትምህርትን መሠረተ ሀሳብን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያዊነት ነፃነት-ወዳድ ባህልንም የሚፃረር ነው። በዚህም ምክንያት ወያኔ የወጣቱን ትውልድ ላይ አዕምሮ ለማላሸቅ የሚነዛውን ፕሮፖጋዳ መቃወም የኢትዮጵያዊያን ሁሉ የዜግነት ግዴታ ነው።

ደግነቱ በአብዛኛዎቹ የስልጠና አዳራሾች እየሆነ ያለው ወያኔ ያሰበውና የተመኘውን አይደለም። የኢትዮጵያ ወጣት የወያኔን ዘረኛ ፕሮፖጋንዳ የሚጋት እንዳልሆነ እያስመሰከረ ነው። በብዙ አዳራሾች የወያኔ ካድሬዎች ሊመልሷቸው ከማይችሏቸው ጥያቄዎች ጋር ተፋጠው እንዲያፍሩ ተደርገዋል። ወጣቶች፣ “የታለ የምታወሩለት እድገት” “ቻይና በሠራው እናንተ የምትፎክሩት ለምንድነው“ “ፍትህ የት አለ” “የአንድ ብሔር የበላይነትን ነው እኩልነት የምትሉት” እያለ ካድሬዎችን እያፋጠጠ ነው። ወጣቱ አፈና በበዛበት ሁኔታ ውስጥም ሆኖ መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን ለማንሳት መድፈሩ፤ በአንዳንድ አዳራሾች ደግሞ በጩኸት የፕሮፖጋንዳውን ሥራ ማወኩ ወጣቱን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ የሚያኮራ ተግባር ነው።

ወያኔ፣ ወጣቱን አድርባይነትን ለማስተማር ያዘጋጀው ስልጠና የወጣቱ ቆራጥነትና አርበኝነት ማሳያ ሲሆን፤ ፍርሃት ለማስፈን የተጠራ ስብሰባ ድፍረትን አደባባይ ሲያወጣ ማየት የሚያኮራ ነው። ወጣቱ በዚህ ስልጠና ላይ ባሳየው ድፍረት ለለውጥ ምን ያህል ዝግጁ እንደሆነ አሳይቷል። አሁን የጎደለው ድርጅት ነው። የወጣቱ ለለውጥ ዝግጁ መሆን አንድ ትልቅ የምሥራች ነው። ይህ ዝግጁነት በድርጅት መደገፍ ደግሞ ተከታትሎ መምጣት ያለበት ሥራ ነው። የወጣቱ የመንፈስ ዝግጅትና ድርጅት ከተቀናጁ የወያኔ ውድቀት ቅርብ ነው።

ወጣቱ ከተቃውሞ ባለፈ ሊሠራቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች ከፊቱ ተደቅነዋል። ከሁሉ አስቀድሞ ድርጅት ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ ሊጤን ይገባዋል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በወያኔ አገዛዝ ሥር ባለችው ኢትዮጵያ ውስጥ ምስጢራዊና ማዕከላዊነትን ያልጠበቁ ትናንሽ ስብስቦች ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ ብሎ ያምናል። ስለሆነም ግንቦት 7፣ እያንዳንዱ ለሀገሩ፣ ለነፃነቱ፣ ለክብሩ፣ ለፍትህ ግድ ያለው ወጣት ከሚመስሉትና ከሚያምናቸው ጥቂት ወዳጆቹ ጋር በምስጢር እንዲደራጅ አጥብቆ ይመክራል። የተደራጁ ስብስቦች ግንቦት 7ን ማግኘት ወይም ግንቦት 7 እነዚህን ስብስቦች ማግኘት አስቸጋሪ አይሆንም። የኢትዮጵያ ወጣት ለለውጥ ዝግጁ ነው። የጎደለው ድርጅት ነው። የጎደለውን ማሟላት ደግሞ የሁላችንም ግዴታ ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በወያኔ ስልጠናዎች ላይ ተቃውሞ ለማሰማት በመድፈራቸው የተሰማውን ደስታ ይገልፃል። ይህ ክስተት ወጣቱ ለለውጥ የተዘጋጀ እንደሆነ በአመላካችነት ወስዶታል። ይህ የለውጥ ፍላጎት በድርጅት ካልታገዘ ውጤት ስለማያመጣ ወጣቱ በትናንሽ ሕዋሶች ራሱን እንዲያደራጅ ይመክራል። ይህንን ካደረግን የወያኔ ፋሺስታዊ አገዛዝን የምናስወግድበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህን ተከትሎ ዕለት በዕለት የስልጠና አዳራሾች በተማሪዎቹ ፉጨት እና ከፍተኛ ተቃውሞ እንደተሞሉ መሆኑታቸው ታውቋል።

የኢትዮጵያን ታሪክ ጥላሸት መቀባት አንዱ የስልጠናው አላማ መሆኑ የተነገረ ሲሆን በተለይም የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንት የኢትዮጵያን ታሪክ ያለፉት 23 አመታት ብቻ እንደሆኑ አድርጎ ለማሳየት ያደረጉት ሙከራ ሙሉ ተቃውሞ እንደገጠመው ታውቋል። በተለይ ህወሃት በአጼ ሚኒሊክ ዘመን የተፈጸሙትን ድረጊቶች እያነሳ የአማራና የኦሮሞን ብሄሮችን ለማጋጨት እየሰራ ነው ሲሉ ተማሪዎቹ ነቅፈዋል። ተማሪዎቹ በጋራ ከናንተ በተሻለ እኛ የአያት ቅድመ አያቶቻችንን ታሪክ እናውቃለን፤ እናንተ የምትነግሩን ታሪክ የጥላቻና ቂም በቀል ታሪክ ስለሆነ አናዳምጣችሁም የሚል መልእክት ማስተላለፋቸውንም የደረሰን መረጃ ያሳያል። በአገሪቱ ስላለው የሰው ልጆች መብት አከባበር ዙሪያ ላይ ባተኮረው የስልጠና ርዕስ ላይም ተማሪዎቹ የፋሽስቱ ወያኔ በአገሪቱ እያካሄደ ያለውን የዘቀጠ የሰው ልጆች መብት አያያዝና አከባበር ማሳያዎቹን በመጠቃቀስ ጉጅሌዎቹ አንገት ማስደፋት መቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በተጨማሪም ከሙስሊሙና ከክርስቲያን ተማሪዎች ከፍተኛ ጥያቄ ያስነሳው የሃይማኖት ጉዳይ ሲሆን፣ ፋሽስቱ ወያኔ በሃይማኖት ጉዳይ እጁን ማስገባቱን፣ የሙስሊም የመፍትሄ አፈላላጊ የኮሚቴ አባላት ያለአገባብ መታሰራቸውን ተማሪዎች ማውገዛቸውን ለማወቅ ተችሏል። አገር በፈጠራ ዶክመንታሪ ድራማ አይመራም የሚሉት ተማሪዎች፣ የሃይማኖት እና የፖለቲካ መሪዎችን ማሰሩ በህዝብ ዘንድ እንዲጠላ ከማድረጉም በተጨማሪ ዋጋ ያስከፍለዋል ሲሉ ተማሪዎች አስጠንቅቀዋል። ነጻ ፕሬስ የሚባል በአገሪቱ ውስጥ እንደሌለም ተጠቅሷል። ተማሪዎቹ በጋራ የፋሽስቱ ወያኔ ለሱዳንና ለጅቡቲ በነጻ የሰጠውን መሬት በማንሳት አገዛዙ መፍትሄ በአፋጣኝ እንዲያመጣ መጠየቃቸውም ታውቋል። ህዝቡ በቀን አንድ ጊዜ ለመብላት በተቸገረበት በዚህ ወቅት በሙስና የተዘፈቁት የጉጅሌዎቹ ሹማምንትና ቅጥረኞች ብቻ ቱጃር መሆናቸውን አመልክተዋል። የየቀኑን የስልጠና ውሎ በተመለከተ የፋሽስቱ ወያኔ ከፍተኛ ሹማምንት በተማሪዎቹ የተሰጡ አስተያየቶችን በመገምገም ሪፖርት ለበላይ አካሎቻቸው እንደሚያስተላልፉ ታውቋል።

## “በሙት መንፈስ የሚመራው የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ”

ህወሃቶች አገሪቷን እየገዙ ያሉት በግምት ነው፡፡ ያውም በእነርሱ አቅምና ችሎታ በተገመተ ግምት፡፡ የግምታቸውም ምንጭ ጎጠኝነታቸውና ስር የሰደደው ጥላቻቸው መሆኑ ደግሞ አገሪቷን የከፋ አደጋ ውስጥ እንድትወድቅ አድርጓታል፡፡ ገደብ በሌለው ዘረኝነታቸውና፤ በቀልን በወለደ ጥላቻቸው ውስጥ ሁነው አብዮታዊ ዲሞክራሲ እያሉ የሚጠሩትን ቅዥታቸውን ለከፍተኛ ተቋም ተማሪዎች እናስተምራለን ብለው እየተደናበሩ እንደሆነ እያየን ነው፡፡ ለዚህ ስልጠና የሚጠፋው ገንዘብ እና ግዜ ከምር ህገ መንግስቱን ለማስከበር ቢውል ኑሮ አገራችን እንደምን ባማረባት ነበር፡፡ የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ግን ከህግ በላይ ነው፡፡ የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ዜጎች በሙሉ እኩል ሁነው እንዲኖሩ ሳይሆን ጥቂቶች ብዙሃኑን ተጭነው፤ ብዙሃኑ ጥቂቶችን ተሸክሞ የሚኖርበት ሥርዓት እንዲዘረጋ የሚያደርግ ነው፡፡ የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ የግለሰብ ስብዕናን አሳልፎ ሰጥቶ የአንድን ጨካኝ ቡድንን ሃሳብ እንደ ኃይማኖት ተቀብሎ መኖር ማለት ነው፡፡

የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ የአገሪቷን ህግ የሚያከብር አይደለም፡፡ አለማክበር ብቻ ሳይሆን የህወሃቱ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሃሳብ አቀንቃኞች ራሳቸውን ከህግ በላይ አድርገው የሚያዩበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ህግ ሲጥሱም ህግ መጣሳቸውን እንደ መብታቸው ይቆጥሩታል እንጂ በገዛ እጃቸው የፃፉትን ህግ አፍርሰው ፍትህን ዋጋ እንዳሳጡት አይሰማቸውም፡፡ ለዚህም ነው የእኛን *“አብዮታዊ ዲሞክራሲ”* ካልተማራችሁ ወደ ትምህርታችሁ አትመለሱም የሚሉት፡፡ እንዲህ ለማለት የሚፈቅድላቸው ህግ ባይኖርም ህወሃቶች ራሳቸውን ከህግ በላይ አድርገው ስለሚቆጥሩ በእነርሱ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ያልታሰረውን ሁሉ መቅጣት መብታቸው እንደሆነ ከልባቸው ያምናሉ፡፡

ህወሃቶች የኑሯቸው መሠረት ደመ-ነፍስ ነው፡፡ ጭንቅላታቸው እንደ ሰው ልጅ ማሰቡን በማቆሙ ሁሉንም ነገር በግብታዊነት ይፈፅሙታል፡፡ ተማሪዎች የመንግስትን ፖሊስ የመማር ወይም ደግሞ ያለመማር መብት ቢኖራቸውም ህወሃቶች ግን የተማሪዎችን መብት ጥሰው አብዮታዊ ዲሞክራሲን ካልጋትናችሁ ዱላ ይከተላል ብለዋል፡፡ ደግነቱ ተማሪዎቹ የህወሃቶቹን ባዶነት የሚያሳዩ ብርቱ ብርቱ ጥያቄዎችን አንስተው እየተሟገቱ ይገኛሉ፡፡ ለጥያቄዎቹም መልስ ከህወሃት መራሹ መንግስት እንደማይጠብቁም ጨምረው ተናግረዋል፡፡ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት እስራት ውስጥ ያሉ ካድሬዎችም ለተማሪዎቹ ጥያቄ በቂ ምላሽ መስጠት አቅቷቸው ከለመዱት ዱላና ዛቻ ራሳቸውን ፈቀቅ ማድረግ ተስኗቸው ሲደናበሩ ታይተዋል፡፡ ካዴሬዎቹ ስለ ህግ የበላይነት ያላቸው ግንዛቤ የተዛባ ነው፡፡ የእነርሱ የህግ የበላይነት የሚመጣው በብርቱ ብረት ካሠራቸው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት እንጂ ከተፃፈው ህግ አይደለም፡፡ የተፃፍው ህግ አብዮታዊ ዴሞክራሲን አንማርም፤ የእናንተንም ስልጠና አንፈልግም የሚሉ ተማሪዎችን ለማጥቂያነት ይውላል እንጂ ዜጎችን በእኩልነት ሊዳኝ አይውልም፡፡

የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ እኩልነትን አያውቅም፡፡ የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ጥቂቶች ብዙሃኑን ተጭነው፤ብዙሃኑም ጥቂቶችን ተሸክመው መከራቸው በዝቶ የሚኖሩበት ሥርዓት ነው፡፡ በህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ቅኝት ውስጥ መግባት ማለት ጥቂት ዘረኞችንና ዘራፊዎችን ተሸክሞ ለመኖር መምረጥ ነው፡፡ በህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ህወሃት ሁሉንም ነው፡፡ ህወሃት ንጉሥ ነው፡፡ ንጉሡ ህወሃት አይከሰስም ሰማይም አይታረስም የሚል የሞተ ፍልስፍና በህወሃት ዘንድ ገዥ አስተሳሰብ ነው፡፡ መሪያቸው የነበረው መለስ ዜናዊ ከአገሪቷ ላይ 3 ቢሊዮን ዶላር መስረቁ እየታወቀ የጠየቀው አልነበረም፡፡ እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ሌባ በህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ፍልስፍና መሠረት ባለ ትልቅ ራዕይ ተብሎ እስከ ዛሬ እየተወደሰ ይገኛል፡፡ የህወሃት አባላትን ዝሪፊያ ሊያስቆም የቻለ የህግ አካል አልተገኘም፡፡ ህወሃቶች ቀዳሚ ተግባር አድርገው የያዙት የአገሪቷን ሃብት እንደ ጠላት ንብረት አድርጎ መዝረፍ ነው፡፡ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የህወሃቶችን ዝሪፊያ ለማስቆም ህይወት ያለው አስተሳሰብ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአገሪቷ መከላከያ ኃይልና የደህንነቱ መሥሪያ ቤት ዋና ዋና የሥልጣን እረከኖች በህወሃቶች ብቻ መያዛቸው የእነርሱ አብዮታዊ ዲሞክራሲ እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል የምትለውን እንስሳ በሰው ልጆች ላይ እንድትስለጥን ያደረገ ነው፡፡ እኛ ከሌለን አገሪቷ ትበተናለች እያሉ የሚያሟርቱት ህወሃቶች እንደ ሰው ልጅ ማሰብ በማቆማቸው መሆኑም መታወስ ይኖርበታል፡፡ ይሄን ከፋት አያደርጉትም ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ እነርሱን ከሌሎች ዜጎች ጋር ከህግ በታች እኩል አድርጎ የሚያስተዳድር ሥርዓት በኢትዮጵያ ከሠፍን አገሪቱ ተበታትና፤ ህዝቢቿም እርስ በርሳቸው ቢተላለቁ ግድ ያላቸው ቡድኖች አይደሉም፡፡ ምኞታቸውም እነርሱ ከላይ፤ ሌላው ህዝብ በሙሉ ከታች ከእነርሱ እግር ሥር ሁኖ እንዲኖር ነው፡፡ ይሄን ምኞታቸውን ቅዥት አድርጎ ማስቀረት ለራሱ ክብር ከሚሰጥ ዜጋ የሚጠበቅ ግዜው የሚጠይቀው የጀግና ተግባር ሁኖ ይጠብቀናል፡፡

የእነዚህ ቡድኖች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ግለሰብን አያውቅም፡፡ የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ የቆመበት መሠረት የግለሰብን ማንነት አጥፍቶ እና የራስን ሥብዕና ትቶ፤ ከአንድ ከተሰወረ አካል ለሚመጣ አስተሳሰብ ያለምንም ጥያቄ ተገዝቶ መኖር በመቻል ላይ ነው፡፡ አስተሳሰቡ ክፉም ይሁን ደግ ተቀብሎ ከማስፈፀም በቀር ለምን ብሎ መጠየቅ ብዙ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ከሰሞኑ ተማሪዎች እንዲቀበሉት እየተገፋፉ ያሉት ሥብዕናቸውንና ግለሰባዊ ማንነታቸውን ለህወሃቶች በምናምን እንዲሸጡላቸው ነው፡፡ አብዮታዊ ዲሞክራሲን ያልሰጠነ ትምህርት ቤት መግቢያ ሰርቲፊኬት አይሰጠውም ብለዋል፡፡ ይሄ ምንም እንኳ ህገ ወጥ ቢሆንም በስውሩ ቡድን ተወስኗልና መፈፀሙ አይቀርም፡፡ ተማሪዎች አምነውና ፈቅደው ሳይሆን ለትምህርታቸው ሲሉ የህወሃቶችን አብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡ የግለሰብን ነፃነት መግፈፍ ከዚህ ይጀምራል፡፡ አደርባይነትን ማስተማር ከዚህ ይነሳል፡፡ ለትምህርታቸው ሲሉ መሆን የማይፈልጉትን ሁኖ መገኘት፡፡በዚህ ድርጊት አገሪቷ ትጎዳለች እንጂ አትጠቀምም፡፡

እንግዲህ የተማሪዎች ነፃነት በዚህ ሁኔታ መገፈፍ ተጀምሯል፡፡ ህወሃት እስካለ ድረስ ይሄ የግለሰቦችን ነፃነት መግፈፍ ማቆሚያ እንደማይኖረው የታወቀ ነው፡፡ የህወሃትን አብዮታዊ ዲሞክራሲ መማር ለምን ግዴታ ሆነ ብለው የሚጠይቁ ሰዎች አሉ፡፡ ምክንያቱ ግልፅ ነው፡፡ የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ በህዝቡ ዘንድ የተጠላ፤ የሙት መንፈስ የሚመራው ህይወት ዓልባ አሥተሳሰብ ስለሆነ ነው፡፡ ይህን በሙት መንፈስ የሚመራውን አስተሳሰብ አስገድዶ ዜጎች ላይ ለመጫን የሚደረገው ከንቱ ድካም አገሪቷን ይጎዳታል እንጂ አይጠቅማትም፡፡ በዚህ ዕርባና ቢስና አማራጭ አልባ ስልጠና ላይ ነገ አገሪቷን ተርክበው የሚመሩ ብዙ ወጣቶች እየተሳተፉ ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ግን ወደ ፊት ለዕነርሱ የምትሆን ማለፊያ አገር እንድትኖራቸው የተሻለውን አማራጭ ለመፈለግ ትግላቸውን ካሁኑ መጀመር አለባቸው፡፡

ህወሃቶች የኢትዮጵያ ችግር የሚፈታው በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብ አላቸው፡፡ዜጎች በሙሉ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማዕከላዊነት እንዲታሠሩ ከልባቸው ያምናሉ፡፡ ለዚህም የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ ይሄ የእኔ አስተሳሰብ ብቻ የሚለው አገሪቷና ትውልዱ አማራጭ አመለካከቶችን እንዳያዩ የሚያግድ ነው፡፡ አብዛኛው ህዝብ የወደደው ሌላ የተሻለ አማራጭ እንኳ ቢኖር የህወሃቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ያንን የተሻለ አስተሳሰብ ለማጥፋት በምድር ላይ ያሉ ወንጀሎችን ሁሉ ለመፈፀም ወደ ኋላ አይልም፡፡ በ1997 ዓ.ም የተደረገውን የቅንጅትን ታሪክ ማስታወስ ብቻ በቂ ይሆናል፡፡

ተማሪዎች ሆይ ስሙን !

ያች አገር ነገ የእናንተ ናት፡፡ እናንተ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የገባችሁት ልትመራመሩ፤ ልዩ ልዩ አመለካከቶችን አገናዝባችሁ የሚሻላችሁን ልትቀበሉ፤ ያልወደዳችሁትን ልትጥሉ ነው፡፡ ይሄን ማድረግ መብታችሁ ነው፡፡ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚባለውን የህወሃቶችን ሙት ፍልስፍና አለመማር ብቻ ሳይሆን መቃወምም ህገ-መንግስታዊ መብታችሁ ነው፡፡ይህ መብታችሁ በዘረኞቹና በዘራፊዎቹ ህወሃቶች ተገፏል፡፡ ህወሃቶች የሚፈልጉት ማንነታችሁን አሳልፋችሁ ለእነርሱ እንድትሰጧቸው ነው፡፡ ማንነታችሁን ለዘረኞቹ አስተሳሰብ አሳልፋችሁ ከሰጣችሁ ሰው መሆናችሁ ይቀርና ሌላ ፍጡር ትሆናላችሁ፡፡ የእኔ የምትሉት አስተሳሰብ የሌላችሁ፤ የግል ስብዕናችሁን ያጣችሁ፤ የዘረኞቹና የዘራፊዎቹ ተላላኪዎች እና የእነርሱ አኗኗሪ ሁናችሁ የምትኖሩ ሁናችሁ ትቀራላችሁ፡፡ በዚህ ብቻ አታበቁም በህወቶቹ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ባቡር ላይ ከተሳፈራችሁ በዚያ ባቡር የገዛ ወገናችሁን እየጨፈለቃችሁ የምትነጉዱ ትሆናላችሁ፡፡በዚህም የህዝባችሁ ጠላት መሆን የሚቀርላችሁ ምርጫ ይሆናል፡፡

እንግዲህ ምርጫው ቀላል እንደማይሆን ይታወቃል፡፡ ህወሃት እንደ ወገን ሳይሆን እንደ ጠላት የሚያስብ መሆኑ ደግሞ ምርጫችሁን ይበልጥ ያከብደዋል፡፡ ስልጠናውን መውሰዳችሁ ትክክል ነው፡፡ በስልጠናው ላይ ያነሳችሁት ጥያቄም ድንቅ ነው፡፡ የወደፊት ዕድል ፈንታችሁ በእጃችሁ ይገኛል፡፡ ዕድል ፈንታችሁን ለዘረኞችና ለዘራፊዎች አሳልፋችሁ የምትሰጡ አትሁኑ፡፡ ኢትዮጵያችን የህግ የበላይነት ተከብሮ ፍትህ የተረጋገጠባት አገር እንድትሆን ሳትታክቱ ሥሩ፡፡ ህወሃቶች ከሁሉ በላይ ሁነው ሁሉንም ረግጠው የሚኖሩበት ሥርዓት እንዲያበቃ ታገሉ፡፡ ከዚያች ድሃ አገር ላይ እየዘረፉ በሚሊየን የሚቆጠር ሃብት ያጋበሱ የህወሃት ባለስልጣናት የሃብታቸው ምንጭ ምን እንድሆነ እንዲጣራ ጠይቁ፡፡ የንፁሃንን ደም በከንቱ እንዲፈስ የሚያደርጉ ባለስልጣናት ለፍርድ እንዲቀርቡ የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ፡፡ አገራችሁ ከአንድ አሳሪ አስተሳሰብ ተላቃ፤ አብዛኛው ህዝብ በመረጠውና በወደደው አስተሳሰብ የምትመራ እንድትሆን ሳታቅማሙ ታገሉ፡፡ ለፍትህ ዘብ ቁሙ፡፡ ለእኩልነት ታገሉ፡፡ ለነፃነት የሚከፈለውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ራሳችሁን አዘጋጁ፡፡ ንፁህና በህግ የምትምራ አገር እንድትኖራችሁ የምር ትታገሉ ዘንድ ግዜው እና አገራችን ያለችበት ሁኔታ ያስገድዳችኋል፡፡ በሙት መንፈስ ከሚመራው አብዮታዊ ዲሞክራሲ አቀንቃኝነት ተጠበቁ፡፡ አበቃን፡፡

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖም የአፍ ወለምታ

**(ኤፍሬም ማዴቦ)**

ባለፈዉ ሰሞን ቻይና አፍሪካ ዉስጥ ሰላሳ አመት በማይሞላ ግዜ ዉስጥ ያደረገችዉ የኤኮኖሚና የፖለቲካ መስፋፋት ያሳሰባቸዉ የአሜሪካዉ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ምነዉ ምን አድርገናችሁና ነዉ ፊታችሁን ያዞራችሁብን ብለዉ ለመጠየቅ በርከት ያሉ የአፍሪካ መሪዎችን ቤተ መንግስታቸዉ ድረስ ጋብዘዋቸዉ ነበር። በዚህ የሃሳብ ልዉዉጥ፤ ምክር፤ የእራት ግብዣና የዋሺንግተን ዲሲን ጉብኝት ባጠቃለለዉ የፕሬዚዳንት ኦባማ ድግስ ላይ በመልካም የዲሞክራሲ ጅምራቸዉ የሚወደሱት የጋናና የደቡብ አፍሪካን መሪዎች ጨምሮ እንመራሀለን የሚሉትን ህዝብ በየቀኑ የሚያስሩት፤ የሚደበድቡትና የሚገድሉት የወያኔ መሪዎችም ተገኝተዋል። በዚህ የመሪዎች ስብሰባ ላይ ጠ/ሚ ደሳለኝ ኃ/ማሪያምን አጅበዉ ከመጡት የወያኔ ሹማምንት አንዱ የዉጭ ጉዳዩ ሚኒስትሩ ዶ./ር ቴድሮስ አድሃኖም ነበሩ። ዶ/ር ቴድሮስ በዋሽንግተን ዲሲ ቆይታቸዉ ብዙዎቻችንን እየዋለ ሲያድር ደግሞ እራሳቸዉንም ግራ ያጋባ የሬድዮ ቃለ መጠይቅ ሰጥተዉ ነበር።

"በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ" የአገራችን ባለቅኔዎች አፉ እንዳመጣለትና እንዳሻዉ የሚናገርን ሰዉ . . . ዋ ተጠንቀቅ በአፍ የሚነገር ነገር ዋጋ ያስከፍላል ለማለት የተረቱት ተረት ነዉ። አዎ! ባለቅኔዎቹ እዉነታቸዉን ነዉ። የሚያዳምጡንን ሰዎች ለማስደሰት ስንል ብቻ አፋችን እንዳመጣ የባጥ የቆጡን የምንዘባርቅ ሰዎች የምንላቸዉ ነገሮች እኛዉ ዘንድ ዞረዉ መጥተዉ መጥፊያችን ሊሆኑ ይችላሉ። በቅርቡ ዋሺንግተን ዲሲ ብቅ ብለዉ የነበሩትን የኢትዮጵያ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖምን ያጋጠማቸዉ ይሄዉ ቢጋዝ አፍ ተናግሮ የመጥፋት ቅሌት ነበር። ዶ/ር ቴድሮስ እዚህ ዋሽንግተን ዲሲ ዉስጥ መንግስታቸዉ የሰራተኛ ደሞዝና የአየር ላይ ወጪ እየከፈለ በሚያስተዳድረዉ ሬድዮ አፋቸዉን ሞልተዉ የተናገሩትን ነገር አዲስ አበባ ተመልሰዉ በፌስ ቡካቸዉ በለቀቁት መልዕክት ለማስተባበል ቢሞክሩም ነገሩ "ከአፍ ከወጣ አፋፍ" ሆኖባቸዉ በስህተት ላይ ስህተት እየፈጸሙ ይገኛሉ።

ሬድዮ አገር ፍቅር በመባል ከሚታወቀዉ ሳምንታዊ ሬድዮ ጣቢያ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖም በእስር ላይ የሚገኙት የድምጻችን ይሰማ መሪዎች የአሜሪካ መንግስት ጓንታናሞ ዉስጥ ካሰራቸዉ የአልቃይዳ አባላት ጋር ግንኙነት እንዳላቸዉ ማረጋገጫ አግኝተናል ካሉ በኋላ የአሜሪካ መንግስት ይህንን ግኑኝነት አስመልክቶ የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን ኢትዮጵያ ድረስ ሄዶ ለማነጋገር ለመንግስታቸዉ ጥያቄ እንዳቀረበ ተናግረዋል። ያልነበሩን ነገር ቢኖር የአሜሪካ መንግስት ባቀረበዉ ጥያቄ መሰረት ቃሊቲ ድረስ ሄዶ የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን ማነጋገሩንና አለማነጋገሩን ብቻ ነዉ።

ዶ/ር ቴዎድሮስ ብቻ ሳይሆኑ እሳቸዉ በአባልነት የሚገኙበት ህወሃት የሚባዉ ድርጅት ሃያ ሦስት አመት ሙሉ እየዋሸ የዘለቀ ድርጅት ነዉና የዶ/ር ቴድሮስ ዉሸት ብዙም ላይገርመን ይችላል። ሆኖም ግን ዶ/ር ቴድሮስ ግማሽ ደቂቃ በማይሞላ ግዜ ዉስጥ ሁለት ቱባ ቱባ ዉሸቶችን ሲዋሹ "ከማንም ጋር አንወግንም፤ የቆምነዉ ለእዉነት ብቻ ነዉ" የሚለዉ የአገር ፍቅር ሬድዮ ጣቢያ አዘጋጅ ካለምንም ተከታይ የማብራሪያ ጥያቄ የዶ/ር ቴድሮስን ቆሞ የሚሄድ ዉሸት እንዳለ ተቀብሎ ጭራሽ ዶ/ር ቴድሮስን ማመስገኑ የወያኔ ስርዐት ዉሸትና ቅጥፈት አገር ዉስጥ ብቻ ሳይሆን በዉጭ አገሮችም ምን ያክል ህብረተሰባችንን እንደበከለ ያሳያል።

የኢትዮጵያን የእስልምና እምነት ተከታዮች ከአልቃይዳ ጋር ማገናኘት እነዚህ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ያነሱትን ህጋዊ የመብትና የነጻነት ጥያቄ ላለመመለስ የሚደረግ አጉል ዉጣ ዉረድ ከመሆኑ አልፎ ማንም ማየትና ማሰብ የሚችል ሰዉ የማይቀበለዉ ከንቱ ቅጥፈት ነዉ። ደግሞም ይብላኝ ለዶ/ር ቴድሮስ አፋቸዉን ላላለጣቸዉ እንጂ ወጣቶቹ የድምጻችን ይሰማ መሪዎችኮ የጓንታናሞ እስር ቤት ሲከፈት ከአልቃይዳ ጋር ግንኙነት መፍጠር ቀርቶ አልቃይዳ የሚባል ነገር መኖሩን እንኳን ሰምተዉ የማያዉቁ አንድ ፍሬ ልጆች ነበሩ።

ሌላዉ የዶ/ር ቴድሮስ ትልቁ ዉሸት የአሜሪካ መንግስት ከአልቃይዳ ጋር የነበራቸዉን ግንኙነት አስመልክቶ የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን የታሰሩበት ቦታ ድረስ ሄዶ ላናግራቸዉ ብሎ ጠየቀን ማለታቸዉ ነዉ። እኔ እንደሚመስለኝ ዶ/ር ቴድሮስ አደስ አበባ ከገቡ በኋላ "ምን ነካኝ" ብለዉ ዉሸታቸዉን በፌስ ቡክ ገጻቸዉ ለማስተባበል የቸኮሉት ደጋግመዉ ወዳጃችን ነዉ ብለዉ በተናገሩት በአሜሪካ መንግስት ስም የዋሹት ዉሸት ከንክኗቸዉ ይመስለኛል፤ አለዚያማ ወያኔም ሆነ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ዶ/ር ቴድሮስ በዋሹ ቁጥር ዉሸታቸዉን የሚያስተባብሉ ቢሆን ኖሮ የወያኔ አገዛዝ መሪዎች ስራቸዉ እየዋሹ ማስተባበል ብቻ ይሆን ነበር።

የሚገርመዉ ዶ/ር ቴድሮስ ከአሜሪካ ተመልሰዉ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ የመጀመሪያዉን አንድ ሳምንት ያሳለፉት አንድም አሜሪካ ዉስጥ የዋሹትን ዉሸት በማስተባበል ሌላ ግዜ ደግሞ ሌሎች አዳዲስ ዉሸቶችን በመዋሸት ነበር። በእርግጥም ዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖም በየአገሩ የሚገኙትን አምባሳደሮቻቸዉን ሰብስበዉ የኢትዮጵያን ህዝብ ከት አድርጎ ያሳቀ ነጭ ዉሸት ዋሽተዋል። ለምሳሌ አሜሪካ ዉስጥ የህዳሴዉ ግድብ ቦንድ ሽያጭ እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ከተናገሩ በኋላ ምክንያቱን ሲገልጹ የአሜሪካ ህግ ለቦንድ ሽያጩ አመቺ አለመሆኑን ገልጸዉ ይህንን ለማሻሻል መንግስታቸዉ ከአሜሪካ መንግስት ጋር አብሮ እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል። መቼም ለራሱ አገር ይህ ነዉ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል ህግ አዉጥቶ የማያወቀዉ እንቅልፋሙ የኢትዮጵያ ፓርላማ የአሜሪካንን መንግስት የሚገዛ ህግ ካላወጣ በቀር ዶ/ር ቴድሮስ አደራ የተጣለባቸዉን የቦንድ ሽያጭ እንዴት አሜሪካ ዉስጥ እንደሚወጡት ባላዉቅም መንግስታቸዉ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ባለበት ቦታ ሁሉ ሁሉ ቦንድ መሸጥ ያልቻለዉ የአገሮቹ ህግ ችግር ፈጥሮበት ሳይሆን ለወገኖቹ መብትና ነጻነት የሚታገለዉ ኢትዮጵያዊ ወንድሞቼንና እህቶቼን እየገደላችሁ የምትሸጡልኝ ቦንድ ባፍንጫዬ ይዉጣ ብሎ እምቢ ስላላቸዉ ነዉ። ይህንን ደግሞ መዋሸት እንጂ እዉነትን ሸፍኖ ማስቀረት ያልቻሉት ዶ/ር ቴድሮስም ከተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ በስተቀር የሁሉም አገሮች የቦንድ ሽያጭ እጅግ በጣም ደካማ እንደነበር ለሰበሰቧቸዉ አምባሳደሮች ተናግረዋል፡፡

ከዶ/ር ቴድሮስ በፊትም ሆነ እሳቸዉ እያሉ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከትዉልድ አገሩ ርቆ የሚኖረዉን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ በጥቅማ ጥቅም እየደለለ ከአገዛዙ ጎን ለማሰለፍ ተደጋጋሚ ጥረቶችን አድርጓል። በተለይ የህዳሴዉን ግድብ ቦንድ ሽያጭና የዕድገትና ትራንስፎርሜሺኑን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የወያኔ/ ኢህአዴግ አገዛዝ ዳያስፖራዉን እንደ ከፍተኛ የዉጭ ምንዛሬ ምንጭ ተመልክቶት ነበር፤ ሆኖም አብዛኛዉ ዳያስፖራ ከአገዛዙ ጎን ተሰልፎ ከሚያገኘዉ ግዜያዊ ጥቅም ይልቅ ዘላቂ የሆነዉን የእናት አገሩን አንድነትና የወገኖቹን ፍትህ፤ ነጻነትና እኩልነት በመምረጡ የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ከዳያስፖራዉ እዝቃለሁ ብሎ የተመኘዉ የዉጭ ምንዛሬ ህልም ሆኖ ቀርቷል።

ሌላዉ የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ከፍተኛ በጀትና የሰዉ ኃይል መድቦ ዳያስፖራዉን ለማማለል በሙሉ ሀይሉ የተንቀሳቀሰበት አካባቢ ቢኖር የከተማ ቦታና ቤት ሽያጭ ዘመቻ ነዉ። በእርግጥ አንዳንድ ከህዝብና ከአገር ጥቅም ይልቅ የራሳቸዉን ጥቅም ያስቀደሙ የዳያስፖራዉ አባላት ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚካሄደዉን የመሬት ቅርምት በይፋ እየተቃወሙ የቅርምቱ ድግስ የእነሱን ቤት ሲያንኳኳ ግን በራቸዉን ወለል አድርገዉ ከፍተዉ የድግሱ ተሳታፊዎች ሆነዋል። አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ግን እናትና አባቴን እያፈናቀላችሁ የምትሰጡኝን መሬትም ሆነ ቤት አልፈልግም ብሎ በቦንድ ሽያጩ ላይ የወሰደዉን ጠንካራ አቋም በከተማ መሬትና ቤት ሽያጭ ላይም ደግሞታል። የወገኖቹን ነጻነትና ፍትህ ለማስከበር በህይወቱ የተወራረደዉን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ የማያወላዉል አቋም ያልተረዱት ዶ/ር ቴድሮስ ግን ያንን የለመዱትን በጥቅማ ጥቅም የመደለል ሴራቸዉን አሁንም እንደቀጠሉበት ነዉ። ለምሳሌ ዳያስፖራዉ በመጪዉ አመት በሚደረገዉ የምርጫ ድራማ ላይ ያለዉን እይታ እንዲለዉጥ ለማድረግ ሲባል ብቻ 40 በ60 በሚባለው የቤቶች መርሃግብር የታቀፉ የዲያስፖራ አባላት የከፈሉበት ቤት የ2007ቱ ምርጫ ከመጀመሩ በፊት በአስቸኳይ ተጠናቅቆ እንዲሰጣቸዉ ትዕዛዝ ተላልፏል። እዚህ ላይ አንድ እጅግ በጣም የገረመኝም ያሳዘነኝም ነገር ቢኖር በአንድ በኩል ግብር ከፋይ በሌላ በኩል ደግሞ ቤት አልባ የሆነዉና እነ ዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖም 99.6% መረጠን የሚሉት አገር ዉስጥ የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ ተረስቶ ትርፍ ቤት ፈላጊዉ ዳያስፖራ ቅድሚያ እንዲሰጠዉ መደረጉ ነዉ።

ለመሆኑ ዶ/ር ቴድሮስና መንግስታቸዉ ሁሌም አክራሪዉ ዳያስፖራ እያሉ የሚያሙትን ማህበረሰብ ወድደዉ ሊስሙት ነዉ ወይን ተጠግተዉ ሊያልቡት እንዲህ የተንሰፈሰፉለት? የዳያስፖራዉን አባት፤ እናት፤ ወንድምና እህት እያሰሩ፤ እየገደሉና የመብትና የነጻነት ጥያቄ የሚያነሳባቸዉን የዳያስፖራ አባል ደግሞ አገርህ አትገባም ብለዉ አገር እየነሱት እነሱ ግን የልመና ኮሮጇቸዉን ተሸክመዉ አሜሪካና አዉሮፓ እየመጡ አገርህን እናሳድግልሃለን ገንዘብ ስጠን ብለዉ የሚጠይቁት በማን አገር ማን ለሚጠቀምበት ልማት ነዉ? እነ ዶ/ር ቴድሮስ እነሱን ከመሰለ ፀረ ህዝብ አገዛዝ ጋር ተመሳጥረዉ የዳያስፖራዉን አባል በህገ ወጥ መንገድ አግተዉ እየደበደቡና መታሰሩን ሰምታ ልትጠይቀዉ የሄደችዉን እህቱን ተወልዳ ካደገችበትና እትብቷ ከተቀበረበት አገር በ24 ሰዐት ዉስጥ ዉጪ ብለዉ እያስገደዱ እንዴት ቢገምቱንና እንዴት ቢመለከቱን ነዉ ዞር ብለዉ እኛኑ ገንዘብ ስጡን ብለዉ የሚጠይቁን? ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፡- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>፡- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን፡፡ g7radio@ginbot7.org

## ወያኔ አክራሪነትን ለመዋጋት አዲስ ስትራቴጂ ነደፍኩ አለ

የህዝብ ዋና ዋና እሴቶች የሆኑትን መብት፤ ነጻነትና እኩልነት ረግጦ አገሪቱን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ በመዉሰድ ላይ ያለዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ እሱ እራሱ ሆን ብሎ በመፍጠር ላይ ያለዉን እክራሪነት ለመዋጋት አዲስ ስታሬቴጂ ነደፉኩ እያለ የተለመደ የቃላት ጫጫታዉን መጀመሩ ተሰማ። ወያኔ አዲሱን ስታሬቴጂ የነደፈዉ ሰበእስልምና፤ በኦርቶዶክስና በፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች ዉስጥ እየታየ ያለው የአክራሪነት አደጋ ለስርዓቱ ፈተኝ ይሆናል በሚል አላማ ስሆን ስትራቴጂዉ በአማራ፣ በኦሮምያና በደቡብ ክልሎች ከመጪው አመት ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

አዲሱ የወያኔ ፀረ አክራሪነት ስትራቴጂ ለአክራሪነት የተጋለጡ ናቸዉ ተብሎ የታመነባቸዉ ዞኖችና ወረዳዎች አመራር አባላት በተገኙበት ዉይይት የተደረገበት ሲሆን በእያንዳንዱ የዉይይት መድረክ ላይ አክራሪ ሀይሎች የአገርና የመንግሰት አደጋዎች መሆናቸዉ በተደጋጋሚ ተገልጿል። በዉይይቶቹ ላይ አገዛዙ እሰካሁን ድረስ አክራሪ ባላቸው ሙስሊሞች ላይ የወሰዳቸዉ እርምጃዎች ተነስተው ዉይይት የተደረገባቸዉ ሲሆን በአማራ አካባቢዎች በተካሄዱት ዉይይቶች ላይ የአማራ ክልል የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ሼህ መሃመድ ሃሰን እንደተገኙ ለማወቅ ተችሏል።

የደቡብ ወሎ አስተዳዳርና ጸጥታ ዘርፍ ም/ል ሃላፊ በውይይቱ ላይ ”ትናንት ያገኘናቸውን መስኪዶች ዛሬ እያጣናቸው ነው፣ በአክረሪው ተይዘው የነበሩትንመስጊዶች ብንወስዳቸውም ተመልሰው ወደ አክራሪዎቹ እየሄዱ ነው።” ነው ብለዋል። ም/ል ሃላፊው አክለውም የሃይማኖት አባቶችን ብቃት ለማሳደግ የፖለቲካአመራሩ እገዛ ማድረግ እንዲሁም በመጪው ምርጫ ድርጅቱ ችግር ውስጥ እንዳንገባ ከአሁኑ እርምጃ መወሰድ አለበት ብለዋል። በስብሰባዎቹ ላይ ለተነሱት ጥያቄዎች የክልሉ አስተዳዳርና ጸጥታ ጉዳዮች ቢሮ ሃላፊ አቶ ደሴ አሰሜ ፣ የርእሰ መስተዳድሩ የከተሞች የህዝብ ግንኙነት አማካሪ አቶደሳለኝ አስራደ፣ የአድማ ብተናና ጸረ-ሽብር ግብረ ሃይል ዋና የስራ ሂደት መሪ ረዳት ኪሚሽነር ደስዮ ደጀን በተጋገዝ መልስ ሰጥተዋል።

ኮሚሽነሩ በኢትዮጵያ ስላለው አክራሪነት በኢህአዴግ አመራር ውስጥ ከፍተኛ ብዥታ እንዳለ ገልጸው፣ የዘመቻ ስራ ካልተሰራ በስተቀር በሚጪው ምርጫ አደገኛሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ሲሉ አስጠንቅቀዋል። ኪሚሽነሩ አክለውም በመጪው ምርጫ ህዝቡ ድንጋይ መወርወሩን ትቶ በዝምታ ሊያልፈው እንደሚችልና ይህምቢሆን ለስርዓቱ ትልቅ አደጋና ውድቀትን ያመጣል ሲሉ አስጠንቅቀዋል የመድረኩ መሪ በበኩላቸው መጅሊሱንና መስጊዶችን ብንቆጣጠራቸውም አክራሪዎችን ህዝቡንበማህበራት ገብተው ይዘውታል ካሉ በሁዋላ ትግሉ ለመጅሊስ ብቻ መተው እንደሌለበትና መንግስት በቀበሌ፣ በአንድ ለአምስት አደረጃጀትና በተለያዩ የተዋረድ ስራዎችገብቶ ስራ ለመስራት መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

## ወያኔ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ለማግባባት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በሹማምንቱ ላይ የቀረበባቸው መራር ተቃውሞ እንዲሁም የማዋረድና የማሸናቀቅ ድርጊት ችላ የማይባሉ ጉዳዮች ናቸው በማለት የተናገረው ቴዎድሮስ አድሃኖ ይህንን ድርጊት ማስቆም ካልቻልን አገዛዙ በውጭ አገራት የሚያደርጋቸው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችም ሆነ ከዲያስፖራው የሚገኘው ከፍተኛ ገቢ ጥያቄ ላይ ይወድቃል ሲል መናገሩን የውስጥ ምንጫችን መረጃ ያሳያል። በስብሰባው ላይ በተለይም ከየ አገራቱ የተሰባሰቡት ሹማምንቱ የግንቦት 7 ዋና ፀሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለፋሽስቱ ወያኔ በህገ ወጥ መንገድ ተላልፈው ከተሰጡ በኋላ በየ አገራቱ ላይ እያስተናገዱት ያለው ተቃውሞ ግራ እንዳጋባቸው ሳይሸሽጉ መናገራቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ችግሩ አፋጣኝ መፍትሄ እንደሚሻም ለጉጅሌዎቹ የበላይ ሹማምንቶች ማሳሰብያ ሰጥተዋል። የውስጥ ምንጫችን እንዳመለከተው በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጉዳይ ላይ በአለማቀፍ ደረጃ የዲያስፖራው ማህበረሰብ እያደረገ ያለው ሰፊ የተቃውሞ ንቅናቄ አገዛዙን ጭንቀት ውስጥ እንደከተተውም አመልክቷል። በስብሰባው መጨረሻም የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንት ከዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ጋር እንዴት መቀራረብ ይቻላል በሚል ሰፊ ውይይት ማድረጋቸው የታወቀ ሲሆን ዲያስፖራውን ለመሸንገል ያስቻላሉ የተባሉ ነጥቦችን በማንሳት አቅጣጫ መሰጠቱንም ለማወቅ ተችሏል።

## የቦሌ መንገዶች በድምጻችን ይሰማ የተቃውሞ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ድረስ በኮብል ስቶን መንገዶች ሳይቀር ድምጻችን ይሰማ፤ ፍትህ እንፈልጋለን፤ ኮሚቴዎቻችን ይፈቱ፤ ጭቆናው ይቁም፤ ግድያው ይቁም፤ የሚሉ የተቃውሞ ጽሁፎች በብዛት ተጽፈውና ተበትነው ማደራቸውን ዘጋቢያችን አመልክቷል። ተመሳሳይ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በተጠናከረ ሁኔታ በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚቀጥሉ ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ ዜና በአዲስ አበባና የክልል ዋና ዋና ከተሞች ህዝቡ የሚቹን የፋሽስቱ ወያኔ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ሙት አመት በግዳጅ እንዲዘክር ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩን ለማወቅ ተችሏል። በአዲስ አበባ በመጭው ረቡዕ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩ የታወቀ ሲሆን የፋሽስቱ ካድሬዎች ለቤት በመዞር የጥሪ ወረቀት በማደል ላይ መሆናቸውንና ህብረተሰቡን በማስፈራራት በቦታው እንዲገኝ ለማድረግ የያንዳንዱን ቤት አባዎራ፤ እማውራና ታዳጊ ወጣት ሳይቀር የሞባይል ስልክ በመመዝገብ ላይ መሆናቸውን ምንጮቻችን አመልክተዋል። ይሁን እንጂ የአገዛዙ ሹማምንት ህዝቡ አይወጣም የሚል ስጋት ውስጥ መውደቃቸውንም ለማወቅ ተችሏል።

## የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የአገራችን ችግሮች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለተማሪዎች በግዳጅ የሚሰጠው ካድሬያዊ ስልጠና ትውልድን የማኮላሸት ሴራ ነዉ ያለዉ ሰማያዊ ፓርቲ ስልጠናዉን በጥብቅ እንደሚቃወም ይፋ ማድረጉ ተሰማ። በዚሁ ሰማያዊ ፓርቲ “ስልጠናዉን አጥብቀንእናወግዛለን!” በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫ፣ ላለፉት 23 ዓመታትህወሓት/ኢህአዴግ ስራዬ ብሎ ካዳከማቸውና ጉዳዬ ከማይላቸው ዘርፎች ውስጥ የሚመደበው የትምህርት ስርዓቱ መሆኑን ገልጾ፣ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸው የገዢው ፓርቲ አባል እንዲሆኑ ሲገደዱ መቆየታቸውና የኢህአዲግ አባል ካልሆኑም ስራሊያገኙ እንደማይችሉ እየተነገራቸው በፍራቻ ለአባልነት የተመዘገቡ ብዙዎች እንደሆኑ የአደባባ ይሚስጥር ነው ብሎአል። በያዝነው ወር በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች ተማሪዎች እንዲሰበሰቡና ስልጠና እንዲወስዱ፣ ስልጠናውን ያልተከታተለም መደበኛ ትምህርቱን እንደማይቀጥል ማስፈራሪያ አይሉት ማሳሰቢያ በገዢው ፓርቲ በኩል መተላለፉንና ተማሪዎቹ በግድ ስልጠናውን እንዲወስዱ መገደዳቸው ሳያንስ ወደ ግቢ ከገቡ በኋላ ተመልሰው መውጣት እንደማይችሉ መደረጉን አስታውሰዋል።

## የዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖም የአፍ ወለምታ

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

ዶ/ር ቴድሮስ ከአገር ፍቅር ሬድዮ ጋር ያደረጉትን ቃለ መጠይቅ ከማጠቃለላቸዉ በፊት ደጋግመዉ የተናገሩት ኢትዮጵያን ምን ያክል እንደሚወዱና ይህ የሚወዱት አገር ህዝብ በእድገት ወደ ፊት ከገፉ አገሮች ተርታ ተሰልፎ ማየት አንደሚቸኩሉ ነዉ። መልካም ምኞት ነዉ። ሆኖም ይህ ምኞት የዚያችን የሚወዷትን አገር ህዝብ ሲናገር አፉን እየዘጉ፤ ሲጽፍ እጁን እያሰሩ፤ ሃሳቡን ሲገልጽ ማዕከላዊ ወስደዉ ሰቅለዉ እየገረፉና ሰላማዊ ሠልፍ ተሰልፎ መብቴንና ነጻነቴን አክብሩልኝ ብሎ የጠየቃቸዉን ደግሞ ደረቱንና ጭንቅላቱን በጥይት እያፈረሱ የሚሳካ ምኞት አይደለም። ዶ/ር ቴድሮስ በአፋቸዉ ብቻ የሚናገሩት ምኞት ዳያስፖራዉ በአፉም በልቡም ዉስጥ ያለ፤ የነበረና ለወደፊትም የሚኖር ምኞት ነዉ።

ምኞታችንናምኞታቸዉ ገጥሞ ኢትዮጵያ አድጋና በልጽጋ የምናያት ግን ዶ/ር ቴድሮስ እኛም እንደሳቸዉ በአገራችን ጉዳይ እንደሚያገባን በዉል ሲረዱና ይህንን ሃያ ሦስት አመት ሙሉ በችንካር ቀርቅረዉ የዘጉብንን በር ወለል አድርገዉ ሲከፍቱ ብቻ ነዉ።

**የኢትዮጵያ ትንሳኤ በልጆቿ መስዋዕትነት ይረጋገጣል!!!!**

ebini23@yahoo.com